
# ምዕራፍ አራት

## ሥነምግባርና የሥነምግባር መርሖዎች




### የሚጠበቁ ውጤቶች


ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፤

- ስለሥነምግባር ምንነትና የሥነምግባር መርሖዎች ደረጃውን የጠበቀ ኢ.ምቋ በመጠቀም ታስረዳላችሁ፤
- መልካም የሆኑና መልካም ያልሆኑ የሥነምግባር ዓይነቶችን በኢ.ምቋ ታስረዳላችሁ፤
- ከሥነምግባር ጋር የተያያዙ የኢ.ምቋ ምልክቶችን ከነሥነምልክታዊ ውበታቸው በዕለት-ተዕለት ተግባቦት ውስጥ ትጠቀማላችሁ፤
- ከንባብ ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሐሳቦችን ትለያላችሁ፤
- የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች በራሳችሁ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢው መንገድ መጠቀም ትጀምራላችሁ፤
- በኢ.ምቋ ሥርዓት የተቃራኒና የተመሳሳይ ምልክቶች አጠቃቀምን በዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በመጠቀም ታሳያላችሁ፤
- የኢ.ምቋ ምልክቶችን ሥነምልክታዊ ባሕርያትን መሠረት በማድረግ ትተነትናላችሁ::

### ቁልፍ ምልክቶች




ቁርኝት




በጎ



ሐቅ




ጥልቅ



መላበስ




ባህሪ




ቁርጠኝነት




አስገዳጅ



መተግበር



ስግብግብነት



ጸያፍ




እርጋታ




ታጋሽነት




ቻይነት




ቸርነት




ጀግንነት




የሥነ ምግባር



ፍትሃዊነት



መርሆዎች




ፈላጭቆራጭ

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ዕይታዊ ንባብ

1. የሚከተለውን ሥዕል በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ አስረዱ።
2. መልካም ሥነምግባር የሚያሳየው ሥዕል የትኛው ነው? ምን ዓይነት መልካም ሥነምግባር ያሳያል?





# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ንባብ

### የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ሥነምግባር ምን ማለት ነው?
2. በክፍላችሁ ወይም በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ መልካም ሥነምግባር አለው/አላት ብላችሁ የምታስቡትን አንድ ተማሪ ወይም መምህር ጥቀሱና ሥነምግባር አለው/አላትለማለት ያበቃችሁን ምክንያቶች አስረዱ
3. አንድ ተማሪ መጥፎ ሥነምግባር አለው የሚባለው ምንን መሠረት አድርጎ ነው?

መምህራችሁ «ሥነምግባርና የሥነምግባር መርሖዎች» የሚለውን ንባብ ሲያነቡ፣፣ ሐሳቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን-ለጎን፣ የምልክት አጠቃቀማቸውን በጥንቃቀቄ ተመልከቱ።

### ሥነምግባርና የሥነምግባር መርሖዎች

ሥነምግባር ማለት በምንኖርበት ማኅበረሰብና አካባቢ ተቀባይነትን ያገኘ መልካም ባሕርን መላበስና መተግበር ማለት ነው። ሥነምግባራችን ከአስተዳደጋችን፣ አኗኗራችንና ከሥነልቡናችን ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ነው። ሥነምግባር ፍላጎታችንና ምርጫችን፣ በጎና ጸያፍ ሥራዎቻችን የሚመነጩበት የማንነት መገለጫ ነው።

የሰው ልጆች በተፈጥሮው፣ እንደሚኖረው አስተዳደግ ማኅበራዊ ገጠመኝና ተጋልጦዎች መልካም ወይም መጥፎ ሥነምግባር ሊላበስ ይችላል። የሰው ልጅ በልጅነት ዘመኑ መልካም የሚባሉ ዓለማዊና መንፈሳዊ ሥነምግባሮችን እንዲያውቅና እንዲተገብር በሚያበረታታ ቤተሰብና ማኅበረሰብ ውስጥ ካደገ ሐቅንና መልካም ነገርን የመውደድና መጥፎ ነገርን የመጥላት ባሕርይን ያዳብራል። መልካም ባሕርይ አንድን ሰው በጎ ተግባራትን ያለማንም አስገዳጅነት እንዲያከናውን ያደርጋል።

እንዲህ ዓይነት ባሕርይ የተላበሰ ሰው የመልካም ሥነምግባር ባለቤት ነው ሊባል ይችላል። ሥነምግባር ከሰው የሚመነጭና ካለማንም አስገዳጅነት የሚፈፀሙ ተግባራት መገለጫ ነው። ለምሳሌ ሆደ ሰፊነትና እርጋታ፣ ታጋሽነትና ቻይነት፣ ቸርነትና ጀግንነት፣ ፍትሐዊነትና በጎነት፣ ወዘተ፣. የመልካም ሥነምግባር መገለጫዎች ናቸው።

በተቃራኒው የሰው ልጆች የባሕርይ ማስተካከያ አሊያም የቤተሰብ ክትትል ካልተደረገለት፣ ወይም በመጥፎ አስተዳደግ ካደገ፣ መጥፎውን መልካም፣ ቆንጆውን ደግሞ የሚያስጠላ አድርጎ የመመልከት ባሕርይ ሊኖረው ይችላል። እንዲህ ዓይነት ሰው አስነዋሪ ተግባራትን ያለምንም እፍረት ይተገብራል፤ ይናገራል። አንድ ሰው፣ አንድን መጥፎ ሥራ በንግግርም ሆነ በተግባር ያለምንም እፍረት የሚናገርና የሚተገብር ከሆነ፣ መጥፎ ሥነምግባርን የተላበሰ ነው እንለዋለን። ከመጥፎ ሥነምግባር መገለጫዎች ውስጥ ተንኮል፣ ሐሰት መናገር፣ ግልፍተኝነት፣ ስግብግብነት፣ እብሪተኝነት፣ ተሳዳቢነት፣ ወዘተ፣ ይገኙበታል።

የሥነምግባር መርሖዎች በጋራ የሚኖሩ ወይም የሚሠሩ ህዝቦች፣ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች በጋራ የሚመሩበት የሚከተሉትና የሚተዳደሩበት ራሳቸውንና ሥራቸውን ለመቆጣጠር የሚያግዙ የሥነምግባር መመሪያዎች ናቸው። የሥነምግባር መርሖዎች እንደ ሀገሩ፣ እንደ ባህሉ፣ እንደ ሙያው ወዘተ፣ ሊለያዩ ይችላሉ። ሆኖም በብዙዎቹ ሕዝቦች፣ ባህሎችና ሙያዎች ተቀባይነት ያላቸው የተወሰኑ መርሖዎች አሉ።

መልካም ሥነምግባር ያለው ዜጋ ለሀገር እድገት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ዛሬ የሀገራችንን እድገት ወደ ኋላ እየጎተቱ ላሉ እንደ ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት እንዲሁም በስልጣን መባለግ ዋንኛ መንስኤ የሥነምግባር ጉድለት ነው። ለማኅበራዊ ሕወይት ጠንቅ የሆኑ እንደ ሌብነት፣ ሱሰኝነት፣ አጭበርባሪነት፣ ስግብግብነት፣ ከመጠን ያለፈ ራስ ወዳድነት ወዘተ፣ የሥነምግባር ጉድለት መግለጫዎች ናቸው። ስለዚህ መልካም ሥነምግባር ያለው ዜጋ ማፍራት ለጤናማ ማኅበራዊ ሕይወትና ለሀገር ብልጽግና ከፍተኛ ሚና አለው። እያንዳዱ መልካም ዜጋ መሆን የሚፈልግ ሰውም የማኅበረሰቡንና የሙያውን የሥነምግባር መርሖዎች አውቆ ማክበርና መተግበር ይጠበቅበታል።

## መልመጃ አንድ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ በኢምቁ መልሱ።**

1. ከምንባቡ ውስጥ ስለሥነምግባር ምንነት፣ መገለጫዎች፣ መልካም የሆኑና መልካም ያልሆኑ ባሕርያትን በመለየት በኢምቁ አስረዱ።
2. የምንባቡን ዋና-ዋና ነጥቦች ዘርዝሩ።

3. የምንባቡን ጠቅላላ መልዕክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ፣ በክፍል ውስጥ በሂምቁ መልሱ።

1. ሥነምግባር ማለት ምን ማለት ነው?
2. የአንድ ሰው ሥነምግባር የዛ ሰው የምን መግለጫ ነው?
3. የአንድን ሰው ሥነምግባር የሚወስኑት ዋና-ዋና ነገሮች ምንድናቸው?
4. የመልካም ሥነምግባር መግለጫዎችን ጥቀሱ
5. የሥነምግባር መርሖዎች ማለት ምን ማለት ነው?
6. የጋራ የሥነምግባር መርሖዎች ከሚባሉት ውስጥ አምስት ምሳሌዎች ጥቀሱ
7. መልካም ሥነምግባር ያለው ዜጋ ለሀገር እድገት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። አብራሩ

## መልመጃ ሦስት

### ዐረፍተ ነገሮች ምሥረታ

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው። በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች በመጠቀም የራሳችሁን የኢ.ምቁ ዐረፍት ነገሮች መሥርቱ።

1. ጥልቅ
2. ቁርጠኝነት
3. አስገዳጅ
4. መተግበር
5. ባሕር

## መልመጃ አራት

### የምልክቶች ተቃራኒ ማሳየት

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው። በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች ተቃራኒ ምልክቶች በክፍል ውስጥ አሳዩ።

ምሳሌ:- ጎበዝ- ሰነፍ

1. ቻይ
2. ቸር
3. ጀግና
4. ታማኝ
5. በጎ

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

## ከምልክቶች አዳዲስ ምልክቶችን መፍጠር

**ምሳሌዎች**

*ታማኝ + ነት = ታማኝነት*

*ታማኝ፡ እምነት ሊሰጠው የሚችል ሰው*

*ታማኝነት፡ እምንት*

ምሳሌዎቹን መሠረት በማድረግ፣ ከሚከተሉት ምልክቶች አዳዲስ ምልክቶች መሥርቱ

1. ታጋሽ
2. ቻይ
3. ቸር
4. ጀግና
5. ሰው

# ክፍለ ትምህርት አራት

## የምልክቶች ትንተና

ቀደም ባሉት ክፍሎች በተማራችሁት መሠረት፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማራችኋቸውን ዋና-ዋና ምልክቶች ትንተና በክፍል ውስጥ አሳዩ።



ስምሳሌ:- **ሐቅ**

1. የእጅ ቅርጽ፡ አመላክች ጣት
2. የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፡ ከአፍ ፊት
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡ ወደ ግራ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡ ወደ ፊት
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡ በመጠኑ ኮስተር ያለ ፊት

### ተቃራኒ ምልክቶች

ተቃራኒ ምልክቶች የምንላቸው እርስ በርሳቸው በሀሳብ የሚቃረኑ ምልክቶች ናቸው።

ምሳሌ:-

መስማማት- መቃወም

መሄድ- መምጣት

መልካም- መጥፎ

ሰፊ - ጠባብ

## መልመጃ ስድስት

ከዚህ በታች ምልክቶችን ወክለው ለቀረቡት ቃላት፣ ከላይ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት፣ ተቃራኒ ሠርታችሁ በክፍል ውስጥ አሳዩ።

1. ማዘን
2. ማክበር
3. መራራ
4. መርካት
5. ማሻሻል

### በትርጉም የተለያዩ ሆነው የሚቀራረቡ የኢምቋ ምልክቶች

አንዳንድ የኢምቋ ምልክቶች በትርጉም የተለያዩ ሆነው፣ በምልክት አደራረግ ተቀራራቢ ናቸው። እነዚህ ምልክቶች ስለሚቀራረቡ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ይመስላሉ እንጂ ልዩነት ግን አላቸው።

ለምሳሌ፡-

- መታመም/በሽታ
- መጠገን/ጫማ
- አፋር/ማበጠሪያ
- ደደብ/ቁጭት
- ኬንያ/ፒያሳ
- መዝናናት/በዓል

## መልመጃ ሰባት

ከላይ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት፣ ከአሥር ያላነሱ በትርጉም የተለያዩ ሆነው ነገር ግን በአደራረግ ተቀራራቢ የሆኑ የኢምቋ ምልክቶች ዘርዝራችሁ አሳዩ።

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## የኢምቁ ሰዋስው ናሙናዎች ልምምድ

ከዚህ በታች የተቀመጡትን ናሙናዎች በጥንቃቄ ከተለማመዳችሁ በኋላ፣ ወደ ምንባቡ በመመለስ በኢምቁ አንብቡ።

**ኢምቁ:** ሥነምግባር ትርጉም ምን- መኖር ሕዝብ አካባቢ መደገፍ መልካም መልካም ባሕር ማወቅ፣ መከተል፣ ተግባር ማድረግ ማለት

**አማርኛ:** ሥነምግባር ማለት በምንኖርበት ማኅበረሰብ ና አካባቢ ተቀባይነትን ያገኘ መልካም ባሕርን መላበስና መተግበር ማለት ነው።

**ኢምቁ:** ሥነምግባር እኛ መተሳሰር ምን ምን ጋር- አንድ ማደግ ሁኔታ እንዴት እንዴት አደገ ሁለት መኖር ሁኔታ ሦስት አእምሮ ሁኔታ- ሦስት መገናኘት ጠንካራ

**አማርኛ:** ሥነምግባራችን ከአስተዳደጋችን፣ አኗኗራችንና ከሥነልቡናችን ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ነው።

**ኢምቁ:** ሥነምግባር የኛ ምን- እኛ ፍላጎት፣ ምርጫ፣ የኛ መልካም ሥራ ወይም መጥፎ ሥራ ምንጭ - እኛ መታወቂያ

**አማርኛ:** ሥነምግባር ፍላጎታችንና ምርጫችን፣ በጎና ጸያፍ ሥራዎቻችን የሚመነጩበት የማንነት መገለጫ ነው።

**ኢምቁ:** ሰው ልዩ ልዩ ምክንያት መልካም ወይም መጥፎ ሥነምግባር መከተል ሊሆን ይቻላል ወሳኝ ምን ማደግ ሁኔታ፣ ልምድ ወዘተ፣

**አማርኛ:** የሰው ልጅ በተፈጥሮው፣ እንደሚኖረው አስተዳደግ ማኅበራዊ ገጠመኝና ተጋልጦዎች መልካም ወይም መጥፎ ሥነምግባር ሊላበስ ይችላል።

**ኢምቁ:** አንድ ሰው ልጅ የሆነ ጊዜ ቤተሰብ ማበረሰብ አብሮ መኖር ማደግ በኋላ መሆን ምን መልካም ሰው ተመሳሳይ መልካም- መልካም መወደድ መጥፎ መጥላት

**አማርኛ:** የሰው ልጅ በልጅነት ዘመኑ በመልካም ቤተሰብና ማኅበረሰብ ውስጥ ካደገ፣ መልካም መልካም ነገሮችን ይወዳል፤ መጥፎ ነገሮችንም ይጠላል።